## *አሪት*

“የገነት ንጉሥ ነኝ!” ሲል፣ ሲንጐራደድ
ሔዋንን ላከና ለአዳም ወጥመድ
ሸኾናውን ጠልፎ በእባብ ገመድ
ከመሬት ላይ ጣለው ከትብያ፣ ከአመድ!
“ና! ተቀጣ!” ብሎ በኲነኔ ፍርድ
መቀመቅ ጨመረው በሞት ሊዋረድ።
ግን ባኀርዩ ሆኖ መሓሪ፣ ወዳድ
ጨክኖ አጨልከነም ነውና ዘመድ
በሣልስቱ ዕለት ሊካፈል መአድ
ከሲዖልው አወጣው ትንሳኤ ውሉድ…

## *ወንጌል*

ስልጣን፣ ክብሩን ትቶ በጠባብ ደረት
መልክ፣ ውበትን አጥቶ፣ በአጭር ቁመት
ፈጣሪ እንደጥጃ ቢወለድ በረት
ከሴት ልጅ ተገኝቶ ሰው የሆነ ዕለት፤
*“በዓለም መከራ ስንንከራተት*
*“የጣልክብን ዕዳ እስከ ሞት ቅጣት*
*“ቅመሰው ፍዳችን መራራ ሓሞት*
*“ያውልህ!”* አሉና ጥፊ አቀመሱት
መቸ ጥፊ ብቻ፣ በስቃይ ሊሞት
በምስማር ቸንከረው በዕንጨት ሰቀሉት…

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**